ቀን Date 03 ታህሳስ 2012

ቁጥር Ref. No ወ11-18/227

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

# The Federal Democratic Republic of Ethiopia
# Ministry of Trade and Industry

በአማራ ብሔራዊ ክልለዊ መንግሥት
ለንግድና ገበያ ልማት ቢሮ
<u>ባህርዳር</u>
በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ለንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ
<u>መቀሌ</u>
በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት
ለንግድ ቢሮ
<u>ፊንፊኔ</u>
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ለንግድ ቢሮ
<u>አዲስ አበባ</u>
በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ለንግድና ገበያ ልማት ቢሮ
<u>ሃዋሳ</u>
በሐረሪ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ለንግድ ልማት ቢሮ
<u>ሐረርጌ</u>
በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር
ለንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ
<u>ድሬዳዋ</u>
በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ለንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ
<u>ሠመራ</u>
በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ለንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ
<u>ጋምቤላ</u>
በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልላዊ መንግሥት
ለንግድ ትራንስፖርትና ኢንዱስትሪ ቢሮ
<u>ጅግጅጋ</u>
በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልለዊ መንግሥት
ለንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ
<u>አሶሳ</u>
በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ለድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
<u>ድሬዳዋ</u>
በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ለንግድ ምዝገባና ፈቃድ ቅርንጫፍ ቁጥር 1 ጽ/ቤት
በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ለንግድ ምዝገባና ፈቃድ ቅርንጫፍ ቁጥር 2 ጽ/ቤት
<u>ባሉበት</u>፣

**ጉዳዩ፡- <u>የተሻሻለውን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ደንብን ተግባር ላይ እንድታውሉ ማሳወቅን ይመለከታል፣</u>**

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥን ቀላል፣ ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ዘመናዊ እና ተደራሽ በማድረግ ሀገራችን ለንግድ ሥራ መጀመር (Strting a Businness) ምቹ ሀገር እንድትሆን የንግድ ሥርዓቱን የሚያስተዳድሩ ህጎችን ማሻሻል በማስፈለጉ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ደንብ ቁጥር 392/2012 ተሻሽሎ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቋል፡፡

በመሆኑም የጸደቀው የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሥራ ላይ የሚውል መሆኑ ይታወቃል፡፡

ነገር ግን ለተገልጋዩ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ሲባል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንቡ የጸደቀ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ይህ ደብዳቤ ከተጻፈበት ቀን ጀምሮ ተሻሽሎ በጸደቀው ደንብ መሰረት አገልግሎት እንዲሰጥ እያሳወቅን የጸደቀውን ደንብ ከዚህ ኮፒ 3 ገጽ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

<u>ግልባጭ</u>፣
- ለክብርት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር
- ለክቡራን ሚኒስትር ዴኤታዎች
- ለንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት

<u>ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u>

☎ +251-551 8025/29
+251-557 5866
✉ 704
Fax: +251-551 3421, 552 3416
+251-553 1027, 554 0286
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

# የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (ማሻሻያ)

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 392/2009ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፣

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 52(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1/ **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ______/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2/ **ማሻሻያ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 5 እና የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 52(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. የደንቡ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (4) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4) ተተክቷል፤

   "4/ በንግድ ማኅበር የንግድ ስም እንዲሻሻል ሲጠየቅ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባዔ፣አግባብ ያለው ባለስልጣን ስለመሻሻሉ ለዚህ በተዘጋጀ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አውታርን በመጠቀም ያሳውቃል፡፡

2. በደንቡ በየትኛውም ቦታ ላይ "አመልካቹ የዋና ስራ አድራሻና የቅርንጫፍ የስራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንኑ የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ " የሚለው ተሰርዞ "አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ በሚል ተተክቷል፡፡
3. አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ረ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (1) ፊደል ተራ (ረ) ተተክቷል

   "ረ/ አመልካቹ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲሁም ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የንግድ ሥራ አድራሻ የአመልካቹ የንግድ ሥራ አድራሻው ነው ተብሎ ይወሰዳል፤ "

4. የደንቡ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል፤

   "2/ ግለሰብ ነጋዴ በውክልና የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀትን ለማውጣት ሲፈልግ ወኪሉ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ የውክልና ማስረጃ ሠነድ ማቅረብ አለበት፤"

5. የደንቡ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ሠ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሠ) ተተክቷል፣



ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

"ሠ/ ለበጀት ዓመቱ ለደመወዝ እና ለሥራ ማስኪያጃ የሚሆን ቢያንስ 100 ሺ/አንድ መቶ ሽህ/ የአሜሪካን ዶላር ወደ አገር ውስጥ በወካዩ ስም ወይም በእንደራሴው ሥም ለማስገባቱ ከባንክ የተሰጠ ማረጋገጫ፤"

6. የደንቡ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 4 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 4 ተተክቷል፡

"4/ ማሻሻያው የሚደረገው በማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ከሆነ የማህበሩ አባላት ማሻሻያ ያደረጉበት ሠነድን ለማርጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ዋና ቅጅ፤ ማሻሻያው ከካፒታል ጋር የሚያያዝ ከሆነ ወይም የአድራሻ ለውጥ ከሆነ ሠነድን ለማርጋገጥ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የማህበሩ ቃለ ጉባኤ ዋና ቅጅ እና የአድራሻ ማሻሻያ ቅጽ ላይ በመሙላት በፊርማው ያረጋገጠው በቅጹ የተመለከተው አድራሻ የንግድ ሥራ አድራሻው፤

7. የደንቡ አንቀጽ 21 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አቀጽ 21 ተተክቷል፡፡

21/ <u>የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ</u>

1/ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማስረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

ሀ/ የሥራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ፖስፖርት ዋናውና አስፈጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ

ለ/ ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና እና ፎቶ ኮፒ፣የወኪሉና የሥራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፖስፖርት አስፈላጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ፣

ሐ/ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማስረጃ

መ/ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን ስረዛ ቃለ ጉባኤ/ዋናውን/ እና የኦዲት ሪፖርት፣

2/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት መሰረዙን ለዚህ ተግባር ያዘጀውን የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አውታር በመጠቀም ያሳውቃል፡፡

8. የደንቡ አንቀፅ 23 ንኡስ አንቀፅ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀፅ 2 ተተክቷል፡፡

"2/ ግለሰብ ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀትን በውክልና ለማዉጣት ተወካዩ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተረጋገጠ የውክልና ስልጣን ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

9. የደንቡ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 6 ፊደል ተራ (መ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (መ) ተተክቷል፤

"መ/ የንግድ ማንበሩ ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዘጋጀው ቅጽ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የንግድ ሥራ አድራሻው፡፡ ይህ አመልካቹ በቅጹ የተመለከተው አድራሻ ቅርንጫፍ የንግድ ሥራ አድራሻው ነው ተብሎ ይወሰዳል፤

10. የደንቡ አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል፤

'2/ የንግድ ማህበር ከሆነ የኦዲት ሪፖርት፤

11. የደንቡ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 3 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተተክቷል፡-



ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

"3/ ማሻሻያው የሚደረገው በማህበሩ የመመስረቻ ፅሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ከሆነ የማህበሩ አባላት ማሻሻያውን ያደረጉበት ሠነድን ለማርጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ዋና ቅጅ ፤ ማሻሻያው ከካፒታል ጋር የሚያያዝ ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ ወይም የአድራሻ ለውጥ ከሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዘጋጀው ቅጽ ላይ ማህበሩ የንግድ ሥራ አድራሻዬ ነው ብሎ የሞላው እና በፊርማው ያረጋገጠው የንግድ ሥራ አድራሻ የአመልካቹ የንግድ የሥራ አድራሻ ነው ተብሎ ይወሰዳል፤

12. የደንቡ አንቀጽ 41 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 41 ተተክቷል፤

1/ የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምስክር ወረቀት ለስረዝ ከማቀርብ ማመልከቻ ቅፅ ጋር የሚከተሉተ መረጃዎች ተየይዘው መቀረበ አለባቸው

ሀ) የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምስክር ወረቀት፣

ለ) የሆልዲንግ ስምምነት ስለመፍረሱ ሰነድነ ለማረጋገጥ በሀግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ፣

ሐ) የሆልዲንግ አስተባባሪ ኪባንያ ሥራ አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውና አስፈላጊ ገጾች ፎቶኮፒ

2/ የሆልዲን ስምምነቱ ስለመፍረሱ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ለዚህ ዓላማ ያዘጋጀውን የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አውታር በመጠቀም ይፋ ያደርጋል።

13. የደንቡ አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል፡-

1/ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ የፍራንቻይዘሩና የፍራንቻይዚ ውል ማፍረሻ ስምምነት ሰነድ፤

14. የደንቡ አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 3 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተተክቷል፤

3/ አምራቾች ወይም አስመጪዎች ከምርት ባህሪያቸው የተነሳ ለችርቻሮ ሽያጭ አስገዳጅነት ያላቸው ምርቶች በችርቻሮ ሊሸጡ ይችላሉ፤

15. ከደንቡ አንቀጽ 52 በኋላ አዲስ አንቀፅ 53 ተጨምሮ ከአንቀጽ 53 እስከ አንቀጽ 55 ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀፅ 54 እስከ አንቀፅ 56 ሆነው ተሸጋሽገዋል።

53/ በዚህ ደንብ ስለመታወቂያ እና ፓስፖርት የተነገሩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የመንጃ ፈቃድ እና ከመሥሪያ ቤቶች የሚሰጡ መታወቂያዎችን በማቅረብም አገልግሎት ይሰጣል፤

3. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከሀዳር 27 ቀን 2012 ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አብይ አህመድ(ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት